የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETTE
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፸፰
አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፪ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No.78
ADDIS ABABA 22nd October, 2014

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፻፳/፪ሺ፯ ዓ.ም

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ማስፈጸሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ………ገጽ ፯ሺ፮፻፹፰

CONTENTS

Regulation No. 320/2014

Information Network Security Agency Re-establishment Proclamation Execution Council of Ministers Regulation…. ………………………………………………Page 7688

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፳/፪ሺ፯

### የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅን ለማስፈጸም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ (በአዋጅ ቁጥር ፰፻፫/፪ሺ፭ እንደተሻሻለው) አንቀጽ ፭ እና አንቀጽ ፴፭ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር ፰፻፰/፪ሺ፮ አንቀጽ ፲፩(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ማስፈጸሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፳/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "አዋጅ" ማለት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፰/፪ሺ፮ ነው፤

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ ስር ለተመለከቱት ቃላት የተሰጡ ትርጓሜዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No 320/2014

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR EXECUTION OF INFORMATION NETWORK SECURITY AGENCY RE-ESTABLISHMENT PROCLAMATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and Article 35 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 (as amended by Proclamation No. 803/2013) and Article 11(1) of Information Network Security Agency Re-Establishment Proclamation No. 808/2013.

### PART ONE
### GENERAL

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Information Network Security Agency Re-establishment Proclamation Execution Council of Ministers Regulation No.320/2014".

2. **Definitions**

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "Proclamation" means the Information Network Security Agency Re-establishment Proclamation No. 808/2013;

2/ definitions provided for under Article 2 of the Proclamation shall be applicable;

፫/ "ኤጀንሲ" ማለት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ነው፤

፬/ "የአባልነት ምዝገባ" ማለት ኤጀንሲው በድረ-ገጽ አማካኝነት የአባልነት ክፍያ በመክፈል ከተለያዩ የደህንነት ተቋማት ጋር ስምምነት በመፈጸም ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ለማግኘት የሚካሄድ ምዝገባ ነው፤

፭/ "የሳይበር ኦፐሬሽን" ማለት የሳይበር መረጃንና ዲጂታል ፎረንሲክ ማስረጃን ለመሰብሰብ፣ ሀገራዊ ደህንነትንና የዜጎች ደህንነትን የሚጎዱ የሳይበር እንቅስቃሴዎችን ለማግታት ወይም በሉአላዊነት ላይ የሚቃጡ የሳይበርና ኤሌክትሮማግኔቲክ ቴክኖሎጂ ጥቃቶችን ለመከላከል በስራ ላይ የሚውል ዘዴ ነው፤

፮/ "ዋና ዳይሬክተር" ማለት የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለኤጀንሲው መረጃዎች፣ ኦዲት እና ግምገማ

### ፫. ስለሚስጥራዊ መረጃዎች

በሌሎች ሕጎች የተደነገገው ቢኖርም ዋና ዳይሬክተሩ፦

፩/ የኤጀንሲውን የሰው ሃይል ፕሮፋይል፣ የተወሰኑ የሂሳብ ሰነዶች፣ መሳሪያዎች፣ አሰራሮች፣ የስራ ውጤቶች እና የእቅድና የስትራቴጂ ሰነዶችን እጅግ ጥብቅ ሚስጥር ብሎ በመሰየም ለማንኛውም አካል እንዳይገለፁ ያደርጋል፤

፪/ ለብሔራዊና ተቋማዊ ደህንነት፣ ለተቋሙ መወዳደር አቅም እና ለሠራተኞቹ ደህንነት አስፈላጊ መሆኑን ሲያምን የኤጀንሲውን ማንኛውም የሥራ ስፍራ፣ ቁሳዊና ኢ-ቁሳዊ የሀብት መረጃዎችንና ሌሎች የቦታ ምልክታ መረጃዎች ጥብቅ ሚስጥር እና ሚስጥር ብሎ በመሰየም ለማንና መቼ ተደራሽ መሆን እንዳለበት በመመሪያ ይወስናል፡፡

### ፬. ስለሂሳብና የክዋኔ ኦዲት

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ የተደነገገው ቢኖርም ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ንብረት በዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር ሙሉ በሙሉ እንዳይመረመር ወይም በከፊል እንዳይመረመር ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ በማዘጋጀት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅርቦ ያፀድቃል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩም በየጊዜው የመረጃውን ሚስጥራዊነት እየፈተሸ መመሪያውን እንዲሻሻል ያደርጋል፡፡

፪/ የኤጀንሲው የውስጥ ኦዲተር ዋና ዳይሬክተሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ የተመለከቱ ሃብቶችን፣ ሰነዶችን እና ሌሎች

3/ "Agency" means the Information Network Security Agency;

4/ "membership registration" means a registration for membership at different security institutions and associations through agreement to obtain various services via website subscription;

5/ "cyber operation" means a technique that is used to exploit cyber intelligence and digital forensic evidence, curb cyber activities that threaten national security and citizen's safety or defend the state sovereignty from an attack by cyber and electromagnetic technologies;

6/ "Director General" means the Director General of the Agency.

## PART TWO
## AGENCY'S DATA, AUDIT AND EVALUATION

### 3. Confidential Data

Notwithstanding the provisions stipulated under other laws, the Director General:

1/ shall restrict the disclosure of employees profile, certain financial accounts, tools, working procedures, outputs, strategic and planning documents to any body by designating them as top secrets;

2/ when he believes it is vital for national security, security of the Agency, its core competencies and its employees' wellbeing, may categorize, through directive the Agency's working places, tangible and intangible assets information and other geographic indicators information as top secret or confidential and determine to whom and when it shall be accessible.

### 4. Financial and Performance Audit

1/ Notwithstanding the provisions stipulated under Article 3 of this Regulation, the Director General may issue a directive, upon approval by the Prime Minister, that entails total or partial restriction of the Auditor General or his representative to audit the Agency's assets. The Prime Minister shall order the amendment of the directive periodically by assessing the secrecy of the data.

2/ The internal auditor of the Agency shall inspect, in accordance with the directive issues by the Director General, the assets, documents and

አስፈላጊ መረጃዎችን ይመረምራል፣ የሂሳብና የክንዋኔ ኦዲት ያካሂዳል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በውስጥ ኦዲተር የሚደረገው የምርመራ ሪፖርት ለዋና ዳይሬክተሩ ብቻ የሚቀርብ ይሆናል።

**፭. የደህንነት ኦዲት**

፩/ ኤጀንሲው ኢንፎርሜሽንና ኮምፒውተርን መሰረት ያደረጉ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ደህንነት ለማረጋገጥ ሲባል በሚያደርገው የደህንነት ተጋላጭነት ኦዲት፣ ጥቅም ላይ ስለሚውሉ ስታንዳርዶች፣ መመዘኛዎች፣ አሰራር ስርዓቶች፣ የደህንነት ኦዲተሮች የሚመሩበት የአፈጻጸም መመሪያ እና የኦዲት ሪፖርት አቀራረብ ስርዓት ይቀርጻል፤ ለኦዲት ተደራጊ ተቋማት አስቀድሞ እንዲያውቁት ያደርጋል።

፪/ የኦዲት ተደራጊ ተቋማት የደህንነት ኦዲት መርሀ ግብር ተቋማቱ ያላቸውን ሀገራዊ ፋይዳና ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ በማስገባት በዋና ዳይሬክተሩ በየጊዜው ይወሰናል።

፫/ ኦዲት ተደራጊ ተቋማት በደህንነት ኦዲት ሪፖርቱ ላይ ማብራሪያ የመጠየቅ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በኤጀንሲው የሚሰጣቸውን ምክረ ሃሳብ መቀበልና የእርምት እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡

፬/ ኦዲት ተደራጊ ተቋማት በራሳቸው የደህንነት ኦዲት እንዲያደርጉ ለማድረግ እንዲችሉ ኤጀንሲው አስፈላጊውን የቴክኒክና ሌሎች ድጋፎችን ማድረግ ይኖርበታል፡፡

**፮. ስለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ደህንነት**

፩/ ኤጀንሲው ሀገራዊ ፋይዳ ካላቸው ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች፣ የኢንፎርሜሽን ማኔጅመንት ስርዓቶችና የጂኦ ስፓሻል መረጃ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ፕሮጀክቶች ሥራ ላይ ከመዋላቸውና ተያያዥነት ያላቸው ግዥዎች ከመፈጸማቸው በፊት፦

ሀ) የፕሮጀክት ጥንስስ ወይም የግዥ ፍላጎት ሂደቱ የደህንነት መመዘኛ ማሟላቱን የማረጋገጥ፣

ለ) ለፕሮጀክቱ ግብአት የሚውሉ ምርቶችና አገልግሎቶች ወይም ሥርዓቶች የደህንነት መመዘኛዎችን አሟልተው መመረታቸውንና በአምራቾቹ ወይም በአገልግሎት ሰጪዎቹ የደህንነት ደረጃውን የጠበቀ የስጋት አመራር የሥራ ሂደት መኖሩን የማረጋገጥ፣

ሐ) ምርቱ፣ አገልግሎቱ ወይም ሥርአቱ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት አስፈላጊ መመዘኛዎችን ማሟላቱን የማረጋገጥ፣

other necessary data stipulated under Article 3 of this Regulation; conduct financial and performance auditing.

3/ The audit report prepared by the internal auditor in accordance with sub-article (2) of this Article shall be submitted only to the Director General.

**5. Security Auditing**

1/ The Agency shall design and notify in a reasonable time to the organization subject to audit about the standards, criteria's, working procedures, security auditor's rule of engagement and audit report presentation system, while it conducts security vulnerability audit to ensure the security of information and computer-based critical infrastructures.

2/ The Director General shall periodically determine the schedule of security audit of organizations subject to audit by considering their national significance and strategic importance.

3/ Without prejudice to their right to seek clarification on the report of security audit, the organizations subject to audit are duty bound to accept the recommendations and to take the necessary measure.

4/ The Agency shall provide the necessary technical and other supports to the organization subject to audit to capacitate them to carry out security audit by themselves.

**6. Information Technology Security**

1/ Prior to the implementation of vital national critical information infrastructures, information management systems and geo-spatial information associated projects and related procurements being made, the Agency shall ensure:

a) the intended project or the procurement process fulfills the security criteria;

b) the satisfaction of the security criteria that the goods, services or systems produced as input for the project or the availability of standard risk management process within the manufacturers or service providers;

c) that the product, service or system meet the necessary criterion prior to make use of it;

መ) የትግበራና ኮንፊግሬሽን ሂደቱ በደህንነት መስፈርቱ መሰረት መከናወኑን የማረጋገጥ፣ እና

ሠ) ቀጣይ የድህረ ትግበራ ሥርአት ደህንነትና የስጋት አመራር መኖሩን የማረጋገጥ፣ ኃላፊነት አለበት።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ለማድረግ የሚመለከታቸው ተቋማት የፕሮጀክት ትግበራ እቅዳቸውንና ተያያዥ ግዥዎችን አስቀድመው ለኤጀንሲው የማሳወቅና የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

፯. **ስለደህንነት ፍተሻና ግምገማ**

፩/ ኤጀንሲው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ (፩) የተመለከቱትን ተግባራት የሚያከናውነው ሀገራዊ ደህንነትንና ብሔራዊ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ስታንዳርድን መሰረት በማድረግ፣ ሳይንስን፣ የፈጠራ እድሎችን፣ የቴክኖሎጂ እድገትን፣ የጋራ ተጠቃሚነትን በሚያበረታታ ሁኔታ እና የተደራጁ ላቦራቶሪዎችን በመጠቀም ይሆናል።

፪/ ኤጀንሲው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ (፩) የተመለከቱትን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችለው መሰረተ ልማት፣ ቴክኖሎጂ፣ የስራ ሂደትና አስፈላጊ ሙያተኞች መኖራቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

፰. **ከሀገር ስለሚወጡና ወደ ሀገር ስለሚገቡ እቃዎች እና ቴክኖሎጅዎች ደህንነት**

፩/ ኤጀንሲው የኢንፎርሜሽንና ኮምፒዩተርን መሰረት ያደረገ ቁልፍ መሠረተ ልማት ደህንነትን ለማረጋገጥ ሲባል ወደ ሀገር ውስጥ መግባትና ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው እና ከሀገር የሚወጡ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ቴክኖሎጂዎችን አስመልክቶ ስታንዳርድና መመዘኛ ያወጣል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀትም ያስፈጽማል።

፪/ ዋና ዳይሬክተሩ ብሔራዊ ደህንነትን ሊጎዳ የሚችል ወይም በፍተሻና ሌሎች ተያያዥ ሂደቶች ምክንያት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ወይም ተያያዥ እቃዎች ወይም ሰነዶች ሚስጥር ሊባክን ይችላል ብሎ ሲያምን ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ ከሀገር የሚወጡና ወደ ሀገር የሚገቡ የኤጀንሲው እቃዎችና ተያያዥ ሰነዶች እንዳይፈተሹ ሊያደርግ ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው በሀገር ውስጥ የተመረቱ ወይም የተሻሻሉ የኢንፎርሜሽንና ሳይበር ደህንነት ቴክኖሎጂዎች፣ የክሪፕቶግራፊክና ኤሌክትሮማግኔቲክ ቴክኖሎጂዎች ለሀገራዊ

d) that the implementation and configuration process is carried out in accordance with the security criterion;

e) the continuity of post implementation security procedure and risk management process;

2/ For the application of sub-article (1) of this Article, the concerned institutions shall cooperate and notify to the Agency their project implementation plan and related procurements.

7. **Security Assessment and Evaluation**

1/ The Agency shall carry out the functions specified under Article 5 (1) of this Regulation in accordance with national security and national information security standards, in a manner that encourages science, innovation opportunities, technological advancement, mutual benefit and by using organized laboratories.

2/ The Agency shall ensure the availability of sufficient infrastructure, technology, work process and necessary professionals that enables it to carry out the functions stipulated under Article 5 (1) of this Regulation.

8. **Export and Import of Products and Security Technologies**

1/ The Agency shall, in order to ensure the security of information and computer based infrastructure, issue standards and criterion regarding information security technologies that can be imported for domestic use and that can be exported and, cause implementation of same in coordination with concerned bodies.

2/ The Director General, with notification to the concerned body, may restrict the inspection of the Agency's product or other related documents to be exported or imported, when he believes that the inspection and other related process may endanger national security by exposing the confidentiality of the information technology or other related products or documents.

3/ Without prejudice to sub-article (2) of this Article, the Director General may issue a directive that prohibits the exportation of certain domestically produced or customized information and cyber security technologies, cryptographic or electromagnetic technologies

ደህንነት ካላቸው ፋይዳ አንጻር ወደ ውጭ እንዳይወጡ የሚከለክል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

**፱. የሳይበር ኦፐሬሽን**

፩/ በሌሎች ሕጎች ለሌሎች አካላት የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ኦፐሬሽንን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል።

፪/ የሳይበር ኦፐሬሽን፡-

ሀ) የሳይበር መረጃንና የዲጂታል ፎረንሲክ ማስረጃን ለመሰብሰብ፣

ለ) በአገር ሉዓላዊነት ላይ የሚቃጡ የሳይበርና የኤሌክትሮ ማግኔቲክ ቴክኖሎጂ ጥቃቶችን ለመከላከል፣ ወይም

ሐ) ብሔራዊ ደህንነትን ወይም የዜጎችን ደህንነት የሚጎዱ የሳይበር እንቅስቃሴዎችን ለማግታት አስፈላጊ መሆኑ ሲታመን፣ በማናቸውም ጊዜ ሊካሄድ ይችላል።

፫/ የሳይበር ኦፐሬሽን፡-

ሀ) በፌደራል መንግስት ትዕዛዝ ወይም በክልል መንግስታት ጥያቄ፤

ለ) በጠቅላይ አቃቤ ህግ ወይም በአቃቤ ህግ ተቋም የበላይ ሃላፊ በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት በፍርድ ቤት በሚሰጥ ትእዛዝ፤ ወይም

ሐ) በኤጀንሲው በራሱ ተነሳሽነት፤

ሊካሄድ ይችላል፤ ሆኖም ኤጀንሲው ለጠየቀው አካል ኦፐሬሽኑ የሚካሄድበትን የጊዜ ገደብ እና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎች አስቀድሞ ያሳውቃል።

፬/ ኤጀንሲው በሳይበር ኦፐሬሽን ሂደት የሚገኙ መረጃዎች ከጠያቂው አካል ውጭ በሌላ አካል እጅ እንዳይገኙ በሚስጥራዊነት እንዲያዙ ይደረጋል።

፭/ ኤጀንሲው የሀገሪቱን የሳይበር ኦፐሬሽን ተግባራት የሚፈጽምበት እና የሚያስፈጽምበት ስርዓት ይቀርጻል።

**፲. ስለዲጂታል ፎረንሲክ**

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው፡-

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፮ (፰) በተደነገገው መሠረት እና በፍርድ ቤት በሚሰጥ ትዕዛዝ መሰረት ከመርማሪ አካላት ጋር በመተባበር የዲጂታል ፎረንሲክ ምርመራ ያካሂዳል፤

based on their significance for national security.

**9. Cyber Operation**

1/ Without prejudice to the powers and duties assigned to other relevant organs in other laws, the Agency shall lead and coordinate national cyber operation.

2/ Cyber operation may be carried out at any time:

a) to collect cyber information and digital forensic evidence;

b) to prevent cyber and electromagnetic attack targeted the national sovereignty; or

c) when it is appropriate to prevent cyber action that threaten the national security or citizen's security.

3/ Upon the prior notification of the time and other relevant information to the requesting body, the Agency shall carry out cyber operation:

a) with the instruction of federal government or by the request of regional governments;

b) by the order of the court upon request by the Attorney General or the head of the concerned prosecution institution; or

c) by its own motion.

4/ The Agency shall ensure the confidentiality of information obtained in the cyber operation process otherwise than in the hand of the requesting body.

5/ The Agency shall design a system to execute and enforce national cyber operation functions.

**10. Digital Forensic**

Without prejudice to the provisions of Article 9 of this Regulation, the Agency shall:

1/ carry out digital forensic investigation in cooperation with relevant investigating bodies pursuant to Article 6 (8) of the Proclamation and by the order of a Court;

፪/ የፍትህ አካላት በራሳቸው የዲጂታል ፎረንሲል ምርመራ አቅም እንዲፈጥሩ እና እንዲያጎለብቱ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል።

**፲፩. ስለመረጃ**

፩/ ኤጀንሲው በአዋጁ አንቀጽ ፮ (፲፬) ወይም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ (፫) መሰረት ከሚሰበስበው መረጃ መካከል ለወንጀል ምርመራ መነሻ የሚሆን መረጃ ካለው ለመርማሪ አካላት ሊሰጥ ወይም በፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል ማስረጃ ካለና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም በአቃቤ ህግ ጥያቄ ሲቀርብ መረጃውን ወይም ማስረጃውን ሊሰጥ ይችላል፤ ሆኖም የመረጃ ምንጮቹና መረጃዎቹ የተገኙባቸውን ዘዴዎች እንዲገልጽ አይገደድም።

፪/ ዋና ዳይሬክተሩ የመረጃ አሰባሰብ፣ ክምችትና ስርጭት እንዲሁም የመረጃ ኦፊሰሮች የሚመሩበት የአሰራር ስርዓት ይቀርፃል፤ የሙያ ስነ ምግባር መመሪያ ያወጣል።

**፲፪. ስለየኮምፒውተር ድንገተኛ አደጋ ምላሽ መስጫ ማዕከል**

ኤጀንሲው ቁልፍ ተቋማት ከብሔራዊ የኮምፒውተር ድንገተኛ አደጋ ምላሽ መስጫ ማእከል ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት፣ ልዩ ልዩ ጥቃቶች ሪፖርት ስለሚደረጉበት ዘዴና ስርዓት እንዲሁም ትስስር በመመሪያ ይወስናል።

**፲፫. ስለ ስታንዳርድ**

፩/ ኤጀንሲው ኢንፎርሜሽንና ኮምፒውተርን መሰረት ያደረጉ ቁልፍ መሰረተ ልማት ደህንነት ኀማረጋገጥ የሚያስችሉ ስታንዳርዶችን የማውጣ ትና አፈጻጸማቸውን የመከታተል ስልጣን ይኖረዋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሰረት የሚወጡ የደህንነት ስታንዳርዶች አስገዳጅ መሆናቸው ወይም አለመሆናቸውን በግልጽ የሚያሳይ ድንጋጌ ማካተት ይኖርባቸዋል።

**ክፍል ሦስት**

**ስለፕሮጀክት አስተዳደር፣ ስለክፍያዎች እና ልዩ ግዥ**

**፲፬. ስለፕሮጀክት አስተዳደር**

፩/ ኤጀንሲው የራሱ የፕሮጀክት የሂሳብ አወቃቀር ስርዓት ይኖረዋል።

፪/ ኤጀንሲው በሀገር ውስጥ በጨረታ ተወዳድሮ ምርት ወይም አገልግሎት አያቀርብም ወይም ፕሮጀክት አይወስድም።

፫/ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ኤጀንሲው የሚያከናውንላቸውን ፕሮጀክቶች ወጭዎች በሙሉ መሸፈን አለባቸው፤ እንደአስፈላጊነቱም

2/ provide the necessary assistance to justice organs to setup and build up their own capability regarding digital forensic investigation.

**11. Intelligence**

1/ The Agency may provide information, among the information obtained pursuant to Article 6 (14) of the Proclamation or Article 9 (3) of this Regulation, to investigative bodies if it finds that the information is appropriate to initiate investigation or present evidences or information upon court order or request of public prosecutor; provided, however, that the Agency shall not be compelled to reveal the sources and the means by which such information or evidence has been obtained.

2/ The Director General shall issue a directive regarding intelligence collection, storage and transmission as well as the rule of engagement and code of ethics to intelligence officers.

**12. Computer Emergency Responding Center**

The Agency shall issue a directive to determine the relation of the critical institutions with the National Computer Emergency Responding Center, the method and systems of reporting various attacks and the coordination's thereof.

**13. Standard**

1/ The Agency shall have the power to issue standards that ensure the security of information and computer based critical infrastructure and to monitor their implementation.

2/ The security standards issued in accordance with sub-article (1) of this Article shall include a provision that clearly states whether or not a certain standard is a compulsory.

**PART THREE**

**PROJECT ADMINISTRATION, PAYMENT AND SPECIAL PROCUREMENT**

**14. Project Administration**

1/ The Agency shall have its own charts of account for projects.

2/ The Agency may not domestically compete in bids for the provision of products, services or to take projects.

3/ Government institutions shall cover whole project costs that the Agency undertakes to perform and, when necessary they may pay

ሙሉውን ወጭ በቅድሚያ ሊከፍሉ ይችላሉ፡፡

፬/ በሌላ ደንብ ወይም መመሪያ የተደነገገው ቢኖርም ወይም በሌላ አኳኋን በአሰራር ተፈፃሚ የሚደረግ የአሠራር ሥርዓት ቢኖርም የመንግስት የልማት ድርጅቶች በኤጀንሲው የሚሰሩላቸውን ፕሮጀክቶች ወጭዎች በሙሉ ወይም በከፊል በቅድሚያ ሊከፍሉ ይችላሉ፡፡

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌን ተፈጻሚ ለማድረግ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ኤጀንሲውን በመወከል በደብዳቤ ዋስትና ሊሰጥ ይችላል፡፡

፮/ ኤጀንሲው የውል ማስከበሪያና የቅድመ ክፍያ ዋስትናዎችን አይጠየቅም፡፡

**፲፭. ስለተመጣጣኝ ክፍያ**

ኤጀንሲው፡-

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፰ (፪) መሰረት የሚሰጡ አገልግሎቶችን እና ምርቶችን ያለምንም የአገልግሎት ክፍያ ለህብረተሰቡ በነፃ ያቀርባል፤

፪/ ለባለ በጀት መስሪያ ቤቶች ለሚሰራቸው ፕሮጀክቶችና ለሚሰጣቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ሙሉ ወጭውን የሚሸፍን ክፍያ ያስከፍላል፤

፫/ ለመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ለግል ቁልፍ መሠረተ ልማቶች ለሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶችና ለሚያቀርበው ምርቶችና አገልግሎቶች ሙሉውን ወጪ የሚሸፍንና ከመደበኛ የገበያ ዋጋ አንጻር ዝቅ ያለ የትርፍ ህዳግን የሚያካትት ክፍያ ያስከፍላል፤

፬/ ለሌሎች ሀገራት ተቋማት የሚሰጡ ምርቶችና አገልግሎቶች ክፍያን በተመለከተ የመንግስትን የዲፕሎማሲ አቅጣጫና ሌሎች ዓላማዎችን ታሳቢ በማድረግ ይወስናል፡፡

**፲፮. ልዩ ግዥ**

፩/ ኤጀንሲው ከኢንፎርሜሽንና ሳይበር ደህንነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውንና ለደህንነት ስጋት ምንጭ ይሆናሉ ብሎ ያመነባቸውን ምርቶችና አገልግሎቶች ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ወይም ውስን አቅራቢዎችን በማወዳደር ግዥ ሊፈጽም ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ኤጀንሲው፡-

ሀ) የመረጃ ትንተናዎችና ሪፖርቶች እንዲሁም የደህንነት ሥልጠና አገልግሎቶች ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ይገዛል፤

ለ) የኢንፎርሜሽንና የሳይበር ደህንነት ተቋማት የአባልነት ክፍያ በቀጥታ ይፈጽማል፡፡

the entire project cost in advance.

4/ Notwithstanding the provisions stipulated in other regulation, directive or customary practices, public enterprises may effect payment of the project cost wholly or partially in advance.

5/ For the application of sub-article (3) of this Article, the Ministry of Finance and Economic Development may issue a guarantee letter on behalf of the Agency.

6/ The Agency may not be required to provide a guarantee for contract performance or advance payment.

**15. Commensurate Fee**

The Agency shall:

1/ supply to the public, without any fee, products and services specified under Article 18 (2) of this Regulation;

2/ require government institutions to cover the entire cost of the project or products and services for which it provides;

3/ require critical private infrastructures or public enterprises to pay the entire cost of the project or products and services, for which it provides, with minimum profit margin as compare to the normal market price;

4/ determine payment for the service and products that it provides for foreign institutions by taking into account government diplomatic directions and other objectives.

**16. Special Procurement**

1/ The Agency may procure services and products, when it believes that it may be a source of security threat and directly related to information and cyber security, from single supplier or through restricted tendering.

2/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, the Agency shall:

a) directly procure from single supplier intelligence analysis and reports as well as security training services;

b) make direct payment for membership of information and cyber security institutions.

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተመለከቱት ግዥዎች የመንግስትን ጥቅም በሚያስጠብቅና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ መንገድ መፈጸም የሚያስችል መመሪያ ያወጣል።

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፯. ስለቅንጅትና ትብብር

ኤጀንሲው፡-

፩/ ከአገር ውስጥ ልዩ ልዩ የደህንነት፣ የሕግ አስከባሪና ሌሎች አጋር ተቋማት ጋር የሚያደርገው ትብብር ኤጀንሲው የተቋቋመበትን ዓላማ በሚያሳካ እና የጋራ ጥቅምን በሚያስከብር መልክ ይሆናል፤

፪/ ከአቻ የውጭ አገር መንግስት ተቋማት፣ የደህንነት ተቋማት ወይም ማህበራት ጋር የሚያደርገው ግንኙነት የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም በሚያስጠብቅና ሉአላዊ የግንኙነት መርሆችን መሰረት ባደረገ መልኩ ይሆናል።

### ፲፰. ስለማህበራዊ ኃላፊነትና ግዴታ

ኤጀንሲው:-

፩/ በሰው ሰራሽም ሆነ በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ለሚኖሩ የመልሶ ማልማትና ግንባታ ስራዎችና ሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በመሳተፍ አቅሙ በፈቀደለት መጠን ኃላፊነቱን ይወጣል፤

፪/ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ የህዝቡን የኢንፎርሜሽንና የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ያዳብራል፤ ፀረ ቫይረስና መሰል ምርቶችንና አገልግሎቶችን ለህብረተሰቡ እንዲደርስ ያደርጋል፤

፫/ ለስራ የሚጠቀማቸው ጨረራ አመንጪ ቴክኖሎጂዎች በአካባቢና በሠራተኞች ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ አቅም በፈቀደ መጠን አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

፬/ ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ፣ በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት እና ለሠራተኞቹ ደህንነት ሲባል የሚያስፈልጉ መኖሪያዎችን ወይም ካምፖችን በሁሉም ኦፕሬሽን ጣቢያዎች ሊገነባ ይችላል።

### ፲፱. ስለሠራተኞች ግዴታ

፩/ በዚህ ደንብ ከአንቀጽ ፬ እስከ ፲ በተመለከቱ ተግባራት የሚሳተፉ ሠራተኞች የአሰራር ስርዓትና አፈጻጸም እና የሙያ ሥነ-ምግባር መመሪያዎችን ተላልፈው የተገኙ እንደሆነ በዲሲፒሊን ተጠያቂ ይሆናሉ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የዲሲፒሊን ቅጣት የወንጀልና ፍትሐ ብሔር ተጠያቂነትን አያስቀርም።

3/ The Director General shall issue a directive that enables protection of the public interest and ensures accountability with respect to direct procurements provided for under sub-article (1) and (2) of this Article.

## PART FOUR
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 17. Integration and Cooperation

The Agency shall:

1/ cooperate with various internal security organs, law enforcement and other relevant institutions in a manner that assists accomplishment of the objectives of its establishment and promote mutual benefits;

2/ interact with relevant foreign government institutions, security institutions and associations in a manner that ensures the protection of the national interest of the country and respect to the principles of sovereign relation.

### 18. Social Obligation and Responsibility

The Agency:

1/ shall discharge its social responsibilities through participation in man-made or natural disaster recoveries, rebuilding works and other social affairs to the extent its capacity permits;

2/ shall design various programs that create public awareness in relation to information and cyber security; provide antivirus and other similar products and services;

3/ shall take appropriate measures, to the extent possible, to prevent harm occurring to its employees and the environment in relation to radiation emitting x-ray technologies it make use of;

4/ may build residence or camps in all its stations in order to fulfill its responsibility led down by law and for the security of its employees; the details to be determined by directive.

### 19. Obligations of Employees

1/ Employees engaged in the activities specified under Articles 4 to 10 of this Regulation shall be subject to disciplinary measures if they contravene rules of engagement and code of ethics.

2/ The disciplinary measures taken pursuant to sub-article (1) of this Article may not relieve from civil or criminal liabilities.

**፳. <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም አግባብ ያለው አካል ይህንን ደንብ በማስፈጸም ረገድ ከኤጀንሲው ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፳፩. <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፪. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

ኤጀንሲው ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፳፫. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፪ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**20. <u>Duty to Cooperate</u>**

All concerned bodies shall have the obligation to corporate with the Agency for the implementation of this Regulation.

**21. <u>Inapplicable Laws</u>**

No regulation or directive may, as far as they are inconsistent with this Regulation, be applicable with respect to matters covered in this Regulation.

**22. <u>Power to Issue Directives</u>**

The Agency may issue directives necessary for the implementation this Regulation.

**23. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 22nd day of October, 2006.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት